# *በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ እቃዎች አወጋገድ ስርዓት*

# *መመሪያ ቁጥር 56/2003*

በተለያዩ ምክንያት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ እቃዎችን በሽያጭ ወይም በማናቸውም ዘዴ ሊተላለፍ ወይም ሊወገድ እንደሚችል በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 31(1) ላይ የተደነገገ በመሆኑ፣

በበባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያሉ የተለያዩ እቃዎች እንደየባህሪያቸው የሚወገዱበትን ስርዓት በግልፅ ማመልከት በማስፈለጉ፣

ባለስልጣኑ በቁጥጥሩ ስር ያሉ የተለያዩ እቃዎችን የሚያስወግድበት መንገድ በመመሪያ፣ አፈፃፀም መመሪያ እንዲሁም ባለስልጣኑ ከሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት /ጅ.ን.አ.ድ./ ጋር ባደረገው ስምምነት ላይ ተበታትነው የሚገኙ በመሆኑና እነዚህን ለአጠቃቀም ምቹ በሆነ መልኩ ማጠቃለል በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 31(8) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ እቃዎች ስለሚወገዱበት ስርዓት የወጣ መመሪያ ቁጥር 56/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. **“የተተወ እቃ”** ማለት በአዋጁ አንቀፅ 10(3) መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአገር ያልወጣ ዕቃ ወይም በአዋጁ አንቀፅ 28(1- 4) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ወይም በአንቀፅ 28(5)

መሰረት የጉምሩክ ስነስርዓት ከተፈፀመበት በኋላ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከጉምሩክ መጋዘን ያልወጣ ዕቃ ነው፡፡

2. **“ባለቤት የሌላቸው እቃዎች”** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 82(3) በተደነገገው መሰረት በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለቤት ወይም ሀላፊ ያልቀረበበት ወይም በፍርድ ቤት ክስ ያልተመሰረተበት እቃ ነው፡፡

3. **“የተወረሰ እቃ”** ማለት በፍርድ ቤት እቃው እንዲወረስ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት እቃ ወይም በአዋጁ አንቀፅ 104 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ በመሰጠቱ ያለ ተጨማሪ ትዕዛዝ የሚወረስ እቃ ነው፡፡

4. **“አደገኛ እቃ”** ማለት ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለእፅዋት ደህንነት ጎጂ በመሆናቸው ወይም በህግ በተወሰኑ ምክንያቶች ሊሸጡ ወይም ከተወሰኑ አካላት ውጪ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው እቃዎች ናቸው፡፡

5. **“የሚበላሹ እቃዎች”** ማለት በባህሪያቸው ምክንያት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመፈፀሙ በፊት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት እቃዎቹ ከመለቀቃቸው በፊት ከጥቅም ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ በባለስልጣኑ የታመነባቸው እቃዎች ናቸው፡፡

6. **“የቁም እንስሳት”** ማለት በባለስልጣኑ የሚያዙ በህይወት ያሉ የቤትም ሆነ የዱር እንስሳት ናቸው፡፡

7. **“በአስተዳደራዊ ውሳኔ አፈፃፀም የተያዙ እቃዎች”** ማለት የወንጀል ጉዳዮችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት እንዲያገኙ በአዋጁ አንቀጽ 107(2) በወጣው መመሪያ መሰረት የተወሰነውን ቅጣት እንዲሁም ቀረጥና ታክስ ባለመከፈሉ ምክንያት የሚወገዱና ለዚሁ አፈፃፀም እንዲውሉ የሚደረጉ እቃዎች ናቸው፡፡

8. **“የከበሩ ማፅድናት”** ማለት በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/02 አንቀፅ 2(24) ላይ እንደተተረጐመው እንደ ፕላቲኒየም፣ ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኢመራልድና ሳፋየር ያለ የከበረ ማዕድን ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን የሚጨምር ነው፡፡

9. **“ገንዘብ”** ማለት የኢትዮጵያ ገንዘብ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 591/00 አንቀጽ 2(6) ላይ እንደተመለከተው በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸው የውጪ ሀገር ገንዘቦችና በውጭ ሀገር ገንዘብ የተዘጋጁ የክፍያ ማዘዣ ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶችና በውጪ ሀገር ገንዘብ የተያዙ የባንክ ሂሳቦች ወይም የሚከፈሉ ወይም በውጪ ሀገር ሂሳብ ወይም የማቻቻል አሰራር የሚደረግባቸው ንብረቶች (የውጭ ምንዛሪ) ነው፡፡

10. **“እቃ ማስተላለፍ”** ማለት ከባህሪያቸው ወይም ከሚሰጡት ጥቅም ጋር በተያያዘ በተወሰኑ መስሪያ ቤቶች በኩል ጥቅም ላይ እንዲውል ለተቆጣጣሪ ወይም አግባብ ለሆኑ መስሪያ ቤቶች እቃዎችን በክፍያ ወይም ያለክፍያ ማስተላለፍ ነው፡፡

11. **“እቃ ማውደም”** ማለት እቃዎችን በማቃጠል፣ በመሰባበር ወዘተ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የማድረግ ተግባር ነው፡፡

12. **“ጨረታ”** ማለት ተጫራቾች ለዕቃው የሚሰጡትን ዋጋ በታሸገ ፖስታ የሚያቀርቡበት ዝግ ጨረታ ወይም ተጫራቾች ለዕቃው የሚሰጡት ዋጋ በግልፅና ከፍ ባለ ድምፅ የሚያቀርቡበትና የመጨረሻውን ከፍተኛ ዋጋ የሰጠ ሰው አሸናፊ የሚሆንበት ግልፅ ጨረታ ነው፡፡

13. **“ድርድር”** ማለት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና በገዢ የመንግስት መ/ቤቶች መካከል የሚደረግ የግዢ ስምምነት ነው፡፡

14. **“ኮሚቴ”** ማለት በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎችን እንዲያስወግድ በባለስልጣኑ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

15. **“የበላይ ሀላፊ”** ማለት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ ወይም በእነዚህ አካላት የሚወከል ሰው ነው፡፡

16. **‘ባለስልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡

17. **“አዋጅ”** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

18. ሌሎች በመመሪያው ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጉምሩክ ስራዎች አፈፃፀም በተለያየ ምክንያት በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር በሚገኙና በሚወገዱ እቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. መሠረቱ

1. የተተው ዕቃዎች፣ የሚበላሹ ዕቃዎች፣ በሽያጭ መወገድ የሚችሉ የቁም እንስሳት እንዲሁም አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠባቸው ዕቃዎች በዚህ መመሪያ መሰረት በጨረታ የሚሸጡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

2. የተወረሱ ዕቃዎች እንዲሁም ባለቤት የሌላቸው ዕቃዎች በዚህ መመሪያ መሰረት በድርድር የሚሸጡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

3. ገንዘብ፣ የከበሩ ማእድናት እንዲሁም ከታሪክ፣ ከቅርስ፣ ከባህል፣ ከኪነጥበብ ወይም ከሳይንስ አኳያ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎች፣ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ዕቃዎች፣ በሽያጭ መወገድ የሌለባቸው የቁም እንስሳት እንዲሁም በተወሰኑ አካላት ብቻ በጥቅም ላይ መዋል የሚገባቸው አደገኛ ዕቃዎች በዚህ መመሪያ መሰረት አግባብነት ላላቸው መስሪያ ቤቶች ሊተላለፉ የሚችሉ ዕቃዎች ናቸው፡፡

4. የተከለከሉ ዕቃዎች ወይም በየትኛውም አካል በጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው አደገኛ ዕቃዎች ወይም በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ትብብር ተመልሰው በምንም መልኩ ጥቅም ሊሰጡ በማይችሉበት መልኩ ይወድማሉ፡፡

## 5. የእቃዎች ማስወገጃ ጊዜ

የእቃዎች ማስወገጃ ጊዜ፡

1. የመጨረሻ ህጋዊ የፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔ እንደተሰጠባቸው ወይም

2. የተተው ዕቃዎች ከሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 28 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልፍ ወይም

3. የሚበላሹ ዕቃዎች፣ የቁም እንስሳት ወይም አደገኛ ዕቃዎች ከሆኑ ወዲያውኑ ወይም

4. ባለቤት የሌላቸው ዕቃዎች የ30 ቀን የማስታወቂያ የጊዜ ገደብ ሲያልፍ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## እቃዎች ስለሚወገዱበት ሁኔታ

### 6. በድርድር የሚሸጡ እቃዎች

ከማናቸውም የህግና የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ጥያቄዎች ነፃ የሆኑ፣ የተወረሱ ወይም ባለቤት የሌላቸው ዕቃዎች በድርድር ይሸጣሉ፡፡

### 7. የድርድር ሽያጭ አፈፃፀም

1. የድርድር ሽያጭ የሚካሄደው ከመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ጋር ይሆናል፡፡ይሁን እንጂ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶቹ ዕቃዎቹን በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ካልሆኑ ዕቃዎቹ በጨረታ እንዲሸጡ ይደረጋል፡፡

2. በድርድር ለሚሸጡ ዕቃዎች አነስተኛ መሸጫ ዋጋ ሆኖ የሚያገለግለው የዕቃው F.O.B ዋጋ ይሆናል፡፡

3. በዚህ መመሪያ መሠረት በቅድሚያ በድርድር የሚሸጡት ዕቃዎች ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች ከሆኑና በዕቃዎቹ ላይ ከሚፈለገው ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት ፈቃድ ማግኘት የማይቻል ከሆነ ባለስልጣኑ ዕቃዎቹን ለነዚሁ ፈቃድ ሰጪ ወይም ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ዕቃዎቹን በድርድር ሊሸጣቸው ይችላል፡፡

### 8. የዝግ ጨረታ ሽያጭ ስርዓት

1. ለጨረታ የሚቀርቡ ዕቃዎች ናሙና በጨረታ ሰነዱ ላይ በተመለከተው ሁኔታ ከሁለት ቀናት ላላነሰ ጊዜ ለተጫራቾች ለእይታ መቅረብ አለበት፡፡

2. የጨረታ ሰነድ፤

ሀ. የዕቃው አይነት፣ ሞዴል፣ ሴሪያል ቁጥር እና ሌሎች መለያዎችን፣

ለ. የዕቃው ክብደት፣ ብዛት፣ መጠን፣

ሐ. ዕቃው ያለበትን ሁኔታ፣

መ. ዕቃው ለእይታ የሚቀርብበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣

ሠ. ጨረታው የሚካሄድበት ቦታ፣

ረ. ተጫራቾች ማሟላት ያለባቸው ግዴታዎች፣

ሰ. ጨረታው የሚከፈትበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣

ሸ. ተጫራቾች ለዋስትና የሚያስይዙት ገንዘብ መጠን፣

ቀ. ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ ዘዴ ካገኘ መስሪያ ቤቱ ጨረታውን መሰረዝ እንደሚችል የሚያካትት ይሆናል፡፡

3. የጨረታ ሽያጭ ከመክፈቻ ቀኑ አስራ አምስት ቀናት አስቀድሞ የመገናኛ ብዙሀንን ሽፋን ማግኘት አለበት፡፡

4. የጨረታ ሰነድ ከተዘጋጀ በኋላ በያንዳንዱ ገፅ ላይ የባለስልጣኑ ማህተም ተደርጉበት በብር 100 (አንድ መቶ ብር) ለተጫራቾቹ ይሸጣል፡፡

5. በጨረታው ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ ሀያ በመቶ ለጨረታ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O እንዲያስይዙ ይደረጋል፡፡

6. ተጫራቾች የሞሉትን የጨረታ ሰነድና የጨረታ ዋስትና በፖስታ በማሸግ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይጨምራሉ፡፡

7. የጨረታ ሳጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚደርሱ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

8. የጨረታ ሳጥኑ በጨረታ ማስታወቂያ ሰነድ ላይ በተጠቀሰው ቦታ ቀንና ሰዓት በተገኙ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ፊት እንደሚከፈት በማስታወቂያ ይገለፃል፡፡ በማስታወቂያው መሰረት በቦታው በተገኙ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ፊት ይከፈታል፡፡

9. ጨረታው ከተከፈተ በኂላ በጨረታ ሰነድ የተሰጠውን ዋጋ መለወጥ ወይም ማሻሻል ወይም ጨረታው ከተከፈተ በኂላ ራሱን ከጨረታ ውድድሩ ማግለል አይቻልም፡፡

10. በጨረታ ለሚሸጥ እቃ የጨረታው ውጤት በኮሚቴው ከፀደቀ የሽያጭ ውል እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

11. በጨረታው ለተሸነፉ ሰዎች ያስያዙት ዋስትና በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊው ያስያዘው ዋስትና ግን ከሽያጩ የሚታሰብለት ይሆናል፡፡

12. የጨረታ ሽያጩ አከፋፈትና አጠቃላይ ሂደቱ በቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡

13. በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ቢኖሩም የቁም እንስሳት እንዲሁም የሚበላሹ እቃዎች እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አንቀፅ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳይጠብቁ አመቺ በሆነ ሥርዓት በጨረታ ሊሸጡ ይችላል፡፡

14. በጨረታ የሚሸጠው ዕቃ ባለቤት ወይም የባለቤቱ ወኪል የሆነ ሰው በማንኛውም መልኩ በጨረታው መሳተፍ አይችልም፡፡

15. በጨረታ ሽያጭ ሥርዓት ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች የንግድ ፈቃድ ያለው፣የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከባለስልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት/ክሊራንስ/ የሚያቀርብ እንዲሁም የግብር መለያ ቁጥሩን የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም በተሽከርካሪ ጨረታ ሽያጭ ላይ ለመሳተፍ ማንኛውም ዕድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆነ ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሳተፍ ይችላል፡፡

16. ባለስልጣኑ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 9. <u>የግልፅ ጨረታ ሽያጭ ስርዓት</u>

1. በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 ፣13፣14፣15 እና 16 ስለ ዝግ ጨረታ ሽያጭ አፈፃፀም የተመለከቱት ድንጋጌዎች በግልፅ ጨረታ በሚሸጡ እቃዎች ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2. የግልፅ ጨረታ ሰነዱ የሚሸጥ ሳይሆን ተሳታፊዎች ሊያዩት በሚችል ግልፅ ቦታ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከሽያጩ በፊት ከሰባት ቀናት ላላነሰ ጊዜ ተለጥፎ የሚቆይ ይሆናል፡፡

3. በግልፅ ጨረታ ሽያጭ የሚሳተፉ ተጫራቾች ጨረታው ከመጀመሩ በፊት ተመዝግበው ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O የሚያሲዙ ሲሆን የሚያሲዙት የዋስትና ልክ ለጨረታ የቀረበውን ዕቃ ሁኔታ እንዲሁም ተሳታፊዎችን የሚያበረታታበትን ሁኔታ በማገናዘብ በኮሚቴው ይወሰናል፡፡

4. በግልፅ ጨረታ ሽያጭ ወቅት ባለስልጣኑ ለጨረታ የቀረበው ዕቃ የመነሻ ዋጋ ያልተወሰነለት መሆኑን ገልፆ ጨረታውን ካስጀመረ በኋላ በተጫራቾች የቀረበውን የመጨረሻ ዋጋ ጎላ ባለ ድምፅ ወይም በድምፅ ማጉያ ያሰማና የጨመረ ከሌለ ከአንድ እስከ ሶስት በመቁጠር ጨረታውን ይዘጋል፡፡

5. የግልፅ ጨረታው ውጤት ለኮሚቴው ቀርቦ እንደፀደቀ ከአሸናፊው ጋር የሽያጭ ውል እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

6. በግልፅ ጨረታ የሚሸጡ እቃዎች በባህሪያቸው ወይም በብዛታቸው ማነስ የተነሳ በዝግ ጨረታ ለመሸጥ አመቺ የማይሆኑ፣ ያገለገሉ እቃዎች ፣ቀረጥና ታክሳቸው ሊሰላ የማይችል ወይም የሌላቸው እቃዎችንና፣ እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች እቃዎች ወይም ለዝግ ጨረታ ቀርበው ገዢ ያላገኙ እቃዎች ናቸው፡፡

7. የግልፅ ጨረታ ሽያጭ አጠቃላይ ሂደት በቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡

8. ለተሸናፊዎች ያስያዙት ዋስትና በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የሚመለስ ሲሆን ለአሸናፊው ግን ከሽያጩ ላይ የሚታሰብለት ይሆናል፡፡

## 10. *<u>መነሻ ዋጋ</u>*

1. በዝግ ጨረታ ለሚሸጡ ዕቃዎች መነሻ ዋጋ ተደርጎ የሚቆጠረው የዕቃው C.I.F ሲሆን የሚሸጠው እቃ ተሽከርካሪ ከሆነ ግን የመነሻ ዋጋው ከተሽከርካሪው የሚፈለገው የቀረጥና ታክስ መጠን ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በዝግ ጨረታ ለሚሸጡ እቃዎች የC.I.F ዋጋ የጨረታ መነሻ ዋጋ ሆኖ የሚያገለግለው ለሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን በእቃው ላይ ለ ሶስተኛ ጊዜ ዝግ ጨረታ የተደረገ እንደሆነ ግን የእቃው መነሻ ዋጋ የእቃው F.O.B ይሆናል፡፡

3. ተሽከርካሪ ለ3ኛ ጊዜ ለዝግ ጨረታ የሚቀርብ ከሆነና የተሽከርካሪው C.I.F ከቀረጥና ታክሱ አነስተኛ ከሆነ ለ3ኛ ጊዜ የመነሻ ዋጋው C.I.F ሲሆን ለ4ኛ ጊዜ ለጨረታ የሚቀርብ ከሆነ ወይም የC.I.F መጠን ከቀረጥና ታክሱ ከፍ የሚል በሚሆንበት ጊዜ የጨረታው መነሻ ዋጋ ኮሚቴው በሚወስነው መሰረት ይሆናል፡፡

## 11. በጨረታ ሊሸጡ ስላልቻሉ ዕቃዎች

በተደጋጋሚ ለሶስት ወይም ለአራት ጊዜ ለጨረታ ቀርበው ያልተሸጡ ተሽከርካሪዎች፣ ለሶስት ጊዜ ለጨረታ ቀርበው ተጫራች ያልቀረበባቸው ዕቃዎች ወይም ተጫራች ቢቀርብም ከመነሻ ዋጋ በታች ዋጋ የቀረበባቸው እቃዎች ኮሚቴው በሚወስነው የመሸጫ ዋጋ መሰረት ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡

## 12. ለተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች የሚተላለፉ እቃዎች

1. በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያሉ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያላገኑ ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች ለተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶቹ በድርድር ሊሸጡ የማይችሉ ከሆነ እንዲወድሙ ይደረጋል፡፡

2. በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያለ ወርቅ እንዲሁም የውጪ ምንዛሪ ለብሔራዊ ባንክ በክፍያ ይተላለፋል፡፡

3. በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያለ ተመን የሌለው ወይም ሊመነዘር የማይችል ወይም ሀሰተኛ ገንዘብ ለብሔራዊ ባንክ ያለክፍያ ይተላለፋል፡፡

4. ከታሪክ፣ ከቅርስ፣ ከባህል፣ ከኪነጥበብ፣ ወይም ከሳይንስ አኳያ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎች፣ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ዕቃዎች እንዲሁም በተወሰኑ አካላት ብቻ በጥቅም ላይ መዋል የሚገባቸው አደገኛ ዕቃዎች ባለስልጣኑ አግባብነት ላላቸው የመንግስት አካላት ያለክፍያ ሊያስተላልፋቸው ይችላል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ የማይረከበው መሆኑን በፅሁፍ ያረጋገጠው ወርቅ ወይም ሌሎች የከበሩ ማዕድናት እንደሁኔታው በጨረታ ሊሸጡ ወይም ለማእድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በነፃ እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡

## 13. የሚወድሙ እቃዎች

1. ባለስልጣኑ አደገኛ ዕቃዎችን፣ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ፈቃድ ያልሰጡባቸውም ሆነ በድርድር ያልገዟቸው እቃዎችን ወይም የተከለከሉ ዕቃዎችን አግባብ ነው በሚለው መንገድ ሊያስወግዳቸው ይችላል።
2. ባለስልጣኑ የሚያወድማቸው ዕቃዎች በሌሎች መስሪያ ቤቶች ትብብር መውደም ያለባቸው ከሆነ ለሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጥሪ በማድረግና ስለ ዕቃው አወጋገድ በማማከር ዕቃዎቹ እንዲወድሙ ይደረጋል።
3. እቃዎቹ በባለስልጣኑ ሊወድሙ የማይችሉ አደገኛ ዕቃዎች ወይም የተከለከሉ እቃዎች ከሆኑ እነዚህኑ ለማውደም ብቁ ለሆኑ መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች ይተላለፋሉ።
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በሌሎች መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች እንዲወድሙ የሚተላለፉ እቃዎችን ለማውደም መስሪያ ቤቶቹ ወይም ድርጅቶቹ የሚያወጡትን ወጪ ባለስልጣኑ ይሸፍናል።

## 14. የከበሩ ማዕድናት አመዘጋገብና አጠባበቅ

1. በባለስልጣኑ የሚያዙ የከበሩ ማዕድናትን በአግባቡ መመዝገብና መጠበቅ የያዘው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊነት ይሆናል።
2. የከበረ ማዕድን ገቢ ሲደረግ መለያ ቁጥር ካለው መለያ ቁጥሩ፣ የመያዣው ዓይነት፣ እሽጉ፣ ክብደቱ ለብቻው ወይም ከነመያዣው መሆኑን መጥቀስ፣ የባለቤቱ ስም የያዥዎች ስም ዝርዝር፣ የተያዘበት ቦታ፣ አስረካቢ፣ ተረካቢ፣ አረካካቢዎች እና ሌሎች መግለጫዎች በሚዘጋጀው ህጋዊ የገቢ ደረሰኝ ላይ በመፃፍ የደረሰኙን አንድ ቅጂ የከበረ ማዕድኑ ለተያዘበት ሰው መስጠት አለበት።
3. የከበረው ማዕድን ክብደት ብቻውን ወይም ከነመጠቅለያው ከሆነ ተረካቢ፣ አስረካቢና አረካካቢዎች በተገኙበት ተመዝኖ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት።

4. የከበሩ ማዕድናት ምንነት፣ የጥራት ደረጃ እንዲሁም ክብደትን የመሳሰሉ አስፈላጊ ሁኔታዎች በሚወሰደው ናሙና መሰረት ይህንን ስራ በብቃት ለማከናወን አግባብ በሆነ አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

5. የከበሩ ማዕድናት እንደተያዙ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የባለስልጣኑ ገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንዲረከበው መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከሚይዘው የወርቅና ሌሎች ማዕድናት ብዛት አንፃር ወደ ባለስልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት መላክ ሳያስፈልገው በዚህ አንቀፅ በተመለከተው መሰረት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

6. ለባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት የሚላኩ የከበሩ ማዕድናት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በወኪሉ በተፈረመ ደብዳቤ ውክልና በተሰጠው ሰራተኛ ሆኖ በአጃቢ መላክ አለበት፡፡

7. በባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በኩል ከህግ ማስከበር ዘርፍ አግባብ ካላቸው የስራ ክፍሎች የተወጣጡ አረካካቢዎች ይኖሩታል፡፡

8. የከበሩ ማዕድናት የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ብሔራዊ ባንክ ወይም እንደሁኔታው ሌሎች አካላት በግዥ እስኪረከቧቸው ድረስ ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከራየው ሳጥን ውስጥ እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

9. ባለስልጣኑ የተከራየው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሳጥን ቁልፍ የባለስልጣኑ ገቢ ሂሳብ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በሚወክለው ሰው እጅ በኃላፊነት የሚያዝ ሆኖ መክፈት የሚቻለው በበላይ ሀላፊው በተፈረመ ደብዳቤና በደብዳቤው የተጠቀሱት ታዛቢዎች በተገኙበት መሆን አለበት፡፡

10. በተሰጠው የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ መሰረት ብሔራዊ ባንክ የከበረ ማዕድኑን ሲረከብ የከበረ ማዕድኑን ለመረከቡ የሚሰጠው ማረጋገጫ ከከበረ ማዕድኑ ገቢ ደረሰኝ ጋር በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፡፡

## 15. የገንዘብ አመዘጋገብና አጠባበቅ

1. በተለያዩ የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያዘውን ገንዘብ መመዝገብና መጠበቅ የያዙት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሀላፊነት ነው፡፡

2. ገንዘብ ሲያዝ አግባብ በሆነ ህጋዊ የገቢ ደረሰኝ ላይ የእያንዳንዱ ገንዘብ አይነት፣ መለያ ቁጥር፣ አስረካቢ፣ ተረካቢ፣ አረካካቢዎች፣የእያንዳንዱ ምንዛሪ መጠን፣ ጠቅላላ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ገንዘቡ በተያዘበት ሰው ስም ህጋዊ ደረሰኝ ተቆርጦለትና ተመዝግቦ አንድ ቅጂ ገንዘቡ ለተያዘበት ሰው መሰጠት አለበት፡፡

3. የተያዘው ገንዘብ የውጭ ምንዛሪ በሚሆንበት ጊዜ ለማጓጓዝ የሚጠይቀውን ጊዜ ሳይጨምር በ48 ሰዓት ውስጥ የባለስልጣኑ ገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንዲረከበው መደረግ አለበት፡፡ የተያዘው ገንዘብ የኢትዮጵያ ብር በሚሆንበት ጊዜ ግን የያዘው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብሩ በተያዘ በ 48 ሰዓት ውስጥ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዲፖዚት አካውንት ውስጥ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከሚይዘው የውጪ ምንዛሪ ብዛት አንፃር የሚይዘውን የውጪ ምንዛሪ ወደ ባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት መላክ ሳያስፈልገው በዚህ አንቀፅ በተመለከተው መሰረት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

4. የተያዘው ገንዘብ የውጪ ምንዛሪ ሲሆን በገንዘቡ ላይ የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ባለስልጣኑ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከራየው ሳጥን ውስጥ ይቀመጣል፡፡ የተያዘው ገንዘብ የኢትዮጵያ ብር በሚሆንበት ጊዜ በባለስልጣኑ የዲፖዚት አካውንት ውስጥ የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ይቀመጣል፡፡

5. በውጪ ምንዛሪ ላይ የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ እንደተሰጠ በውሳኔው መሰረት ገንዘቡ ለብሔራዊ ባንክ ይተላለፋል፡፡ በተመሳሳይም በተያዘው የኢትዮጵያ ብር ላይ በሚሰጥ የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ መሰረት የተያዘው ብር አግባብ በሆነ አሰራር ወደ መንግስት ካዝና ፈሰስ መደረግ አለበት፡፡

6. ባለስልጣኑ የተከራየው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሳጥን ቁልፍ የባለስልጣኑ ገቢ ሂሳብ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በሚወክለው ሰው እጅ በኃላፊነት የሚያዝ ሆኖ መክፈት የሚቻለው በበላይ ሀላፊው በተፈረመ ደብዳቤና በደብዳቤው የተጠቀሱት ታዛቢዎች በተገኙበት መሆን አለበት፡፡

7. በተሰጠው የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ መሰረት ብሔራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሪውን ሲረከብ የውጪ ምንዛሪውን ለመረከቡ የሚሰጠው ማረጋገጫ ከውጪ ምንዛሪው ገቢ ደረሰኙ ጋር በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## የእቃዎች ርክክብና የሽያጭ ገንዘብ ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ

### 16. የሽያጭ ገንዘብ ገቢ ስለሚሆንበት ጊዜ

1. በዚህ መመሪያ ለተለያዩ አካላት በድርድር የሚሸጡ ዕቃዎችን የሽያጭ ገንዘብ ገዢዎች እቃውን በተረከቡ እስከ አርባ አምስት ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ክፍያ መፈፀም አለባቸው፡፡

2. የጨረታው አሸናፊ ማሸነፉ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በአምስት የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ያሸነፈበትን ዕቃ ዋጋ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የጨረታ አሸናፊው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡

3. በድርድር ለተሸጡ ዕቃዎች በተገለፀው ጊዜ ገንዘቡን ገቢ ያላደረገ ገዢ በንዑስ አንቀፅ አንድ የተገለፀው የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ ባለው ከፍተኛ ምጣኔ ወለድ ይታሰብበታል፡፡

### 17. ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ገቢ የሚያደርጉበት ጊዜ

1. ብሔራዊ ባንክ የከበረውን ማዕድን ከተረከበ በኋላ ባለው አሰራር በአለም የገበያ ዋጋ መሰረት የከበረውን ማዕድን ገንዘብ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ዲፖዚት ወይም ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

2. ብሔራዊ ባንክ ባለው አሰራር መሰረት የሚረከበውን የውጪ ምንዛሪ ባለው የውጪ ምንዛሪ መጠን መሰረት የምንዛሪውን ገንዘብ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ዲፖዚት ወይም ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 18. የተሸጠ ዕቃ ርክክብ

1. በጨረታ ሽያጭ ዕቃ የገዛ ሰው ገንዘቡን ገቢ ባደረገ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ዕቃውን መረከብ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም እቃው የሚገኝበትን የቦታ ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሸጠውን ዕቃ የመረከቢያ ጊዜ እስከ ሃያ ቀናት ሊራዘም ይችላል፡፡
3. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን ያልተረከበ ሰው ለዕቃው የከፈለው ዋጋ ለመንግስት ገቢ ሆኖ ሀቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡
4. በጨረታ ለተሸጠ ዕቃ የመጋዘን ኪራይ አከፋፈል በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀፅ 30(1) (ሐ) በተደነገገው መሰረት ዕቃው ከተሸጠበት ጊዜ ጀምሮ ገዢው እስከሚረከበው ድረስ ለቆዩበት ጊዜ ይሆናል፡፡

## 19. ባለስልጣኑ ገንዘቡን የሚይዝበትና የሚያስተዳድርበት ሁኔታ

1. ባለስልጣኑ ለአጠባበቅ ምቹ ባለመሆናቸው የሸጣቸው የሚበላሹ ዕቃዎች ወይም የቁም እንስሳት ወይም የተተው ዕቃዎችን ወይም በአስተዳደራዊ ውሳኔ አፈፃፀም የሚሸጡ ዕቃዎችን በማስወገድ የሚገኘን ገንዘብ በአዋጁ አንቀጽ 31(6) የተዘረዘሩት የቀረጥና ታክሱ ሂሳብ፣ ሽያጩን ለማከናወን የወጣው ወጪ፣ የመጋዘን ኪራይ እና ዕቃውን ለመጓጓዝ የወጣው ወጪ እንደቅደም ተከተሉ ለመክፈል ከዋለ በኋላ የሚተርፈውን ገንዘብ በባንክ ዲፖዚት ወይም በአደራ ሂሳብ እንዲቀመጥ በማድረግ ለባለመብቱ ተመላሽ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለባለመብቱ ተመላሽ እንዲደረግ የተቀመጠው ገንዘብ እንዲመለስለት ባለመብቱ ሽያጩ በተፈፀመ በ6 ወር ውስጥ ካልጠየቀ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

## 20. የሽያጭ ገንዘብ እንዲመለስ ስለመጠየቅ

1. በዚህ መመሪያ አፈፃፀም በተወገደ ዕቃ ላይ ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያለው ሰው ወይም የዕቃው ባለቤት ተራፊ ገንዘብ በሚኖረው ጊዜ ዕቃዎቹ

መሸጣቸውን በማረጋገጥ ተራፊው ገንዘብ እንዲመለስለት ዕቃው በተሸጠ በ6 ወር ውስጥ ለባለስልጣኑ በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፡፡

2. ኮሚቴውም በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ የቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር ጥያቄ አቅራቢው ባለመብት መሆኑንና ጥያቄው የቀረበው በተገቢው ጊዜ መሆኑን በማረጋገጥ ተመላሽ ሊሆንለት የሚገባ ተራፊ ገንዘብ ሲኖር ተመላሽ እንዲደረግለት ይወስናል፡፡ በዚህም መሰረት ተመላሽ የሚሆነው ገንዘብ ወዲያውኑ ለጥያቄ አቅራቢው ይከፈላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ እቃ አስወጋጅ ኮሚቴ

### 21. ኮሚቴ ስለማቋቋም

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቁጥጥሩ ስር ያሉ ዕቃዎችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

### 22. የኮሚቴው አደረጃጀት

1. ኮሚቴው

   ሀ. አንድ ሰብሳቢ

   ለ. ሶስት አባላትና

   ሐ. አንድ ፀሀፊ ይኖሩታል፡፡

2. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለበላይ ሀላፊው ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል፡፡
4. የማንኛውም የኮሚቴው አባል በበቂ ምክንያት የስራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በሰየመው አካል ከአባልነት ሊነሳ ይችላል፡፡

## 23. የኮሚቴው አሰያየም

1. የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ እንዲሁም አባላት በበላይ ሀላፊው ይሰየማሉ፡፡
2. የኮሚቴው አባላት

   ሀ. ከመጋዘን የስራ ሂደት

   ለ. ከምርመራ ቡድን

   ሐ. ከሌላ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት አለው ከሚባል የስራ ክፍል

የተወጣጡ ይሆናሉ፡፡

## 24. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

1. በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎችን እንደየባህሪያቸው አመቺ በሆነ መንገድ እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡
2. በሌሎች መስሪያ ቤቶች ድጋፍ መውደም ያለባቸው ዕቃዎችን ለማውደም ለሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጥሪ በማድረግ ዕቃዎቹን ያስወግዳል፡፡
3. ለሌሎች ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች መተላለፍ ያለባቸው እቃዎች የሚተላለፉበትን ሁኔታ በማመቻቸት እቃዎቹ እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡
4. በጨረታ የተሸጠው ዕቃ የሚገኝበትን የቦታ ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት የመረከቢያ ጊዜው እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡
5. በሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጉን ይቆጣጠራል፡፡
6. ለዕቃው ባለቤት ተራፊ ገንዘብ የሚመለስ ከሆነና ባለቤቱ ተራፊ ገንዘብ እንዲመለስለት በህግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ካቀረበ ይህንኑ በመመርመር መመለስ ያለበትን የገንዘብ መጠን አስመልክቶ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ገንዘቡ እንዲመለስለት ጥያቄ ያቀርባል፡፡
7. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 (13) እና በአንቀፅ 9(1) ላይ በተመለከተው መሰረት የቁም እንስሳት እንዲሁም የሚበላሹ ዕቃዎችን በተቻለ ፍጥነት እንዲወገዱ ለማድረግና አመቺና

የተፋጠነ የጨረታ ስነስርዓትን በማመቻቸት እነዚህ ዕቃዎች በተለየ ሁኔታ በፍጥነት የሚሸጡበትን ሥነስርዓት ያመቻቻል፡፡

8. ለጨረታ የቀረበውን ዕቃ ሁኔታ እንዲሁም ተሳታፊዎችን የሚያበረታታበትን ሁኔታ በማገናዘብ በግልፅ ጨረታ ለሚሸጡ እቃዎች ተጫራቾች ማስያዝ ያለባቸውን የዋስትና ልክ ይወስናል፡፡

9. የተሽከርካሪዎቹ የC.I.F ዋጋ ከቀረጥና ታክሱ በሚበልጥበት ጊዜ ወይም ለ4ኛ ጊዜ ለዝግ ጨረታ የሚቀርቡ ከሆነ የተሽከርካሪውን የመነሻ ዋጋ ይወስናል፡፡

10. ዕቃዎቹ ተይዘው እንዲወገዱ የተደረገው ለባለስልጣኑ በቀረበ ጥቆማ መሰረት ከሆነ ዕቃዎቹ ሲወገዱ የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ዕቃዎቹ በተወገዱ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋል፡፡

11. የማንኛውንም ዕቃ አወጋገድ በተመለከተ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤ የእቃ አወጋገድና የኮሚቴውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተመለከተም ለበላይ ሀላፊው በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

12. ስራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25. የተለየ የዕቃ አወጋገድ ሥርዓት

በዚህ መመሪያ በተመለከተው ስርዓት ሊወገድ የማይችል ወይም በመመሪያው ከተመለከተው በተለየ ስርዓት ቢወገድ የተሻለ እንደሚሆን በባለስልጣኑ የሚታመንበት ዕቃ ካለ ኮሚቴው ይህንን ዝርዝር ሁኔታ ለበላይ ሀላፊው በማቅረብ በበላይ ሀላፊው ውሳኔ መሰረት አመቺ በሆነ ስርዓት እንዲወገዱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 26. ቀሪ ወጪዎች

ከዕቃው ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ባለስልጣኑ ከባለቤቱ ላይ የሚፈልገውን ገንዘብ ለመሸፈን በቂ ካልሆነ ወይም ዕቃው የወደመ ከሆነና ባለስልጣኑ ዕቃውን ለማውደም ወጪ

የሚያወጣ ከሆነ የዕቃው ባለቤት ለቀረው ገንዘብ ወይም ለማውደም ለወጣው ወጪ ሀላፊ ይሆናል፡፡

## 27. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

በ 1996 ዓ.ም የወጣው በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ባለቤት የሌላቸው ፣ የተወረሱ፣ የተተው፣ ወይም በኮንትሮባንድ የተያዙ ዕቃዎች አሻሻጥና አወጋገድን ለመወሰን የወጣው መመሪያ እንዲሁም በኮንትሮባንድ የተያዘ የውጭ ሀገር ገንዘብ እና የከበሩ ማዕድናት አጠባበቅና አወጋገድ አፈፃፀም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 28. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በባለስልጣኑ ቁጥጥር ስር ያሉና መወገድ ያለባቸው ዕቃዎች በዚህ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

## 29. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል::

**አዲስ አበባ-------------------ቀን 2003 ዓ.ም**

**መላኩ ፈንታ**

**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**